የካምብሪጅ
ከተማ



# ጊዜያዊ የአደጋ ጊዜ መጠለያ
# በጦርነት የመታሰቢያ መዝናኛ ማእከል

## ከከንቲባው እና ከከተማ ሥራ-አስኪያጁ የተሰጠ መልእክት:

በአፕሪል 3፣ የማህበረሰብ ጤና ኮሚሽነሩ ዶ/ር አሳድ ሳያ እና የከተማው ስራ አስኪያጅ የጦርነት መታሰቢያ የሆነውን መዝናኛ ማዕከል፣ የመስክ ቤቱንና ጋራጁን ጊዜአዊ የአደጋ ጊዜ መጠለያ ለማድረግ የሚያግዘውን ትዕዛዝ ተፈራርመዋል።

ይህ መጠለያ የማህበረሰባችን አባላት ለሆኑትና የመኖሪያ ቤት ለሌላቸው ወይም በኮቪድ-19 ምክንያት ራሳቸውን በአግባቡ ማግለል ለማይችሉት በጣም አስፈላጊ የሆነውን የቤትና ጤና እንክብካቤ አገልግሎቶችን ይሰጣል። ይህንን መጠለያ በስራ ላይ ማዋል መጠለያውን ለሚገለገሉት ደንበኞች፣ የጤና እንክብካቤን ለሚሰጡት ሰራተኞች፣ ለመጀመሪያ መላሾችና ለሰፊው የካምብሪጅ ህብረተሰብ መካከል የኮቪድ-19 ስርጭትን ለመቀነስ በጣም አስፈላጊ ነው። በዚህ ፕሮጀክት ዙሪያ ላሳያችሁት ድጋፍ ከወዲሁ አስቀድመን ልናመሰግናችሁ እንወዳለን።

በአካባቢው ላይ ሊከሰት የሚችለውን ተፅእኖ እና ጉዳት መቀነስ እንዲሁም በይዞታው ላይና በዙሪያ ለሚገኘው ማህበረሰብ ጥበቃ መስጠት ከዚሁ ተልዕኮ ጋር የኛ ዋነኛው ስራችን እንደሆነ በተጨማሪ ልናረጋግጥላቹ እንወዳለን።

መጠለያውን በተመለከተ ጥያቄዎች ወይም ስጋቶች ካሏችሁ እባካችሁን cambridgema.gov/covid19 ይጎብኙ በተጨማሪ ደግሞ 24 ሰዓት በሚሰሩት የስልክ መስመሮች አሊያም በኢሜል ያግኙን።

- ከንቲባ Sumbul Siddiqui እና የከተማው ስራ-አስኪያጅ Louis A. DePasquale

## ለአዳዲስ ዜናዎችና መረጃዎች:

ይጎብኙ www.cambridgema.gov/covid19 መጠለያውን በተመለከተ በተደጋጋሚ ለሚነሱት ጥያቄዎች የተሰጡትን መልሶችና አዳዲስ መረጃዎች እንዲሁም ተጨማሪ ጥያቄዎችና ስጋቶች ካሏችሁ ደግሞ ለሚያገኟቸውን ሰዎች አድራሻዎች። ስለኮቪድ 19 አዳዲስ ዜናዎች፣ በበሽታው ስለተያዙ የሰዎች ቁጥር ብዛት፣ የማህበረሰብ ጤና ስለሚያወጣቸው መመሪያዎችና የበለጠ መረጃዎች በተጨማሪነት ያገኛሉ።

ጥያቄዎች ወይም ስጋቶች:

24 ሰዓት የሚሰሩ የስልክ መስመሮች: 617-349-9770

ኢሜይል: 311@cambridgema.gov